# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# ትምህርት ሚኒስቴር

# FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
## Ministry of Education

**መመሪያ ቁጥር 991/2016**

**የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቋም እና የፕሮግራም እውቅና አሰጣጥ መመሪያ**

**__የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቋም እና የፕሮግራም እውቅና አሰጣጥ ለመወሰን የወጣ መመሪያ__**

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የትምህርት ሚኒስቴር ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**__ክፍል አንድ__**

**__ጠቅላላ ድንጋጌዎች__**

**፩. __አጭር ርዕስ__**

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቋም እና የፕሮግራም እውቅና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 991/2016 "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. __ትርጓሜ__**

በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 እና በደንብ ቁጥር 515/2014 የተሰጡት ትርጓሜዎች እንዳሉ ሆነው በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ

**__Content__**

**Directive No. 991/2024**

**Directive for Higher Education institutions` Institutional and Program Accreditation**

***__A Directive for Higher Education institutions` institutional and Program accreditation__***

In accordance with artcle 19 sub article 4 of proclamation No1263/2021, by the powers and responsibilities of the FDRE executive bodies, the ministry of education declared this directive.

***__Part one__***

***__General provisions__***

*1.* ***__Short title__***

This directive shall be cited as "A Directive for Higher Education institutions` institutional and Program accreditation directive number 991/2024"

*2.* ***__Definitions__***

Notwithstanding interpretations stipulated on Higher Education Proclamation No. 1152/2011 and Council of Ministers' Regulations No. 515/2022, unless the context requires otherwise:

1/ **"Regulation"** shall mean the

ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩/ **"ደንብ"** ማለት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 515/2014 ነው፤

፪/ **"የተቋም ዕውቅና"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት መስክ ፈቃድ አግኝቶ ሲሰራ የቆየ ተቋም በባለስልጣኑ ለተቋም ዕውቅና የወጣውን የጥራት ስታንዳርድ ስለማሟላቱ ወይም ባለስልጣኑ በደንብ ቁጥር 515/2014 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 8 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ባለስልጣኑ በወከለው አካል ተገምግሞ ለተቋም የሚሰጥ የጥራት ማረጋገጫ ነው፤

፫/ **"የፕሮግራም ዕውቅና"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት መስክ ፈቃድ አግኝቶ ሲሰራ የቆየ ፕሮግራም በባለስልጣኑ ለፕሮግራም ዕውቅና የወጣውን የጥራት ስታንዳርድ ስለማሟላቱ ባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ በወከለው አካል ተገምግሞ የሚሰጥ የጥራት ማረጋገጫ ነው፤

፬/ **"የተቋም እውቅና እድሳት"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት መስክ ዕውቅና አግኝቶ ሲሰራ የቆየ ተቋም በባለስልጣኑ ለተቋም ዕውቅና እድሳት የወጣውን

Regulation No 515/2022, issued by the Councils of Ministers to determine the structure, power and functions of the Education and Training Authority.

2/ **"Institutional Accreditation"** shall mean a quality assurance accorded to a licensed institution that has been working in the higher education sector as evaluated by the authority or according to the Council of Ministers' Regulations No. 515/2022, article 6, sub-article 8, by an external body delegated by the authority to recognize that the institutional accreditation quality standards established by the authority are met.

3/ **"Program Accreditation"** shall mean a quality assurance accorded to a program that has been licensed to involve in the higher education sector as assessed by the authority or an external body delegated by the authority to recognize that the program accreditation quality standards established by the authority are met.

4/ **"Institutional Re-Accreditation"** shall mean a quality assurance accorded to a licensed institution that has been working in the higher education level as re-assessed by the authority or an external body delegated by the authority to ensure that the quality standards established by the authority for institutional re-accreditation

የጥራት ስታንዳርድ ስለማሟላቱ ባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ በወከለው አካል ተገምግሞ ለተቋም የሚሰጥ የጥራት ማረጋገጫ ነው፣

፭/ **"የፕሮግራም እውቅና እድሳት"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት መስክ ዕውቅና አግኝቶ ሲሰራ የቆየ ፕሮግራም በባለስልጣኑ ለፕሮግራም ዕውቅና እድሳት የወጣውን የጥራት ስታንዳርድ ስለማሟላቱ ወይም ባለስልጣኑ በወከለው አካል ተገምግሞ ለፕሮግራም የሚሰጥ የጥራት ማረጋገጫ ነው፣

፮/ **"የእውቅና አሰጣጥ"** ማለት ለተቋምና ለፕሮግራም እውቅና ወይም እውቅና እድሳት ለመስጠት የሚደረግ ሂደትን በሙሉ ያካተተ ነው፤

፯/ **"የእውቅና አሰጣጥ ካውንስል"** ማለት በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰየም፣ የተቋም እና የፕሮግራም እውቅና ሪፖርት እና የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ የሚያጸድቅ አካል ነው፤

፰/ **"ገምጋሚ ባለሙያ"** ማለት በተቋም እና በፕሮግራም እውቅና ግምገማ ላይ የሚሳተፍ የባለስልጣኑ የእውቅና አሰጣጥ ባለሙያ ነው፤

፱/ **"ተባባሪ ገምጋሚ ባለሙያ"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያስተምር፣ በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የሚሰራ፣ የሙያ ማህበራት አባላት

are met.

5/ **"Program Re-accreditation"** shall mean a quality assurance process in which a program that has been licensed to engage in the higher education sector is assessed by the authority or an external body delegated by the authority to ensure that the quality standards established by the authority for the program re-accreditation are met.

6/ **"Accreditation process"** shall encompass the entire process undertaken to conduct institution and program accreditation or re-accreditation.

7/ **"Accreditation Council"** shall mean an accrediting body nominated by the Director General of the authority to investigate and approve institutional and program accreditation reports and decisions thereto.

8/ **"Assessor"** shall mean an accreditation expert of the authority participating in the assessment of institutional and program accreditation.

9/ **"Co-Assessor"** shall mean an expert teaching at a higher education institution, working in the various industries, have membership in professional association and trained by the authority to take part in institutional and program accreditation along with the authority's accreditation experts.

የሆነ እና በባለስልጣኑ ስልጠና ወስዶ ከእውቅና አሰጣጥ ባለሙያዎች ጋር በመሆን አንድን ተቋም ወይም ፕሮግራም ለመገምግም የሚሳተፍ ነው፤

፲/ **"ግለ-ግምገማ ሪፖርት"** ማለት በባለስልጣኑ የወጣውን የተቋም ወይም የፕሮግራም ስታንዳርድ መሰረት በማድረግ ተቋም ወይም ፕሮግራም ራሱን ገምግሞ ለባለስልጣኑ የሚያቀርበው ሰነድ ነው፤

፲፩/ **"የጥቅም ግጭት"** ማለት በገምጋሚ ቡድኑ ወይም በውሳኔ ሰጪው አባል እና በተገምጋሚው ተቋም መካከል የተቋም ወይም የፕሮግራም እውቅና ግምገማን ገለልተኛ ሆኖ እንዳያከናውን ሊያደርግ የሚችል ሁኔታ ነው፤

፲፪/ **"እውቅናን ማቋረጥ"** ማለት ተቋሙ የእውቅና ወይም የእውቅና እድሳት ሂደቱን ጀምሮ በመሀል በራሱ ፍላጎት ሲያቋርጥ ነው፤

፲፫/ **"እውቅናን መሰረዝ"** ማለት ተቋሙ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን የትምህርት ጥራት መስፈርቶችን ማጓደሉ በባለስልጣኑ ሲረጋገጥ ነው፤

፲፬/ **"ልዩ ግምገማ"** ማለት ተቋሙ እውቅና ወይም እውቅና እድሳት ካገኘ በኂላ በስርአተ ትምህርቱ ላይ ለውጥ/ማሻሻያ ሲያደርግ ወይም በተቋሙ ላይ ቅሬታዎች ሲቀርቡ በባለስልጣኑ

10/ **"Self Evaluation Report"** shall mean a document prepared by HEIs evaluating performance of their institution against institutional and program standarads put in place by the authority and submit the report to the authority.

11/ **"Conflict of Interest"** shall mean a relational condition which negatively affects the impartiality of the assessment process of the institutional and/or educational program accreditation process, as manifested between the institution seeking accreditation and the team of assessors participating in the evaluation process.

12/ **"Withdrawal of accreditation"** shall mean a situation where an institution withdraws from the process of accreditation or renewal of accreditation at its own will, after getting into the process.

13/ **"Canceallation of accreditation"** shall mean suspension of accreditation certificate awarded to HEIs by the authority, where the HEIs is proven to have failed to maintain the standards stated in this directive.

14/ **"Special Assessment"** shall mean an accreditation assessment conducted by the authority when there is a major modification of the curriculum or valid complaints about the program after the

የሚደረግ ግምገማ ነው፤

፲፭/ **"ውስን ግምገማ"** ማለት ተቋሙ ወይም ፕሮግራሙ በሁኔታ የተገደበ እውቅና ወይም እውቅና እድሳት ካገኘ በኋላ በተጓደሉ መስፈርቶች ላይ በባለስልጣኑ የሚደረግ ግምገማ ነው፤

፲፮/ **"እውቅና ሰጪ አካል"** ማለት የትምርትና ስልጠና ባለስልጣን ወይም በባለስልጣኑ ተገምግሞ እውቅና መስጠት እንዲችል ውክልና የተሰጠው የሙያ ማህበር ወይም ተቋም ነው፤

፲፯/ **«ሰው»** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፰/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፤

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ በሚገኙ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## ስለ እውቅና አሰጣጥ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊት፣ ስታንዳርድ እና የአሠራር ሂደት

**፬. <u>ስለ እውቅና አሰጣጥ</u>**

፩/ ማንኛውም የእውቅና መስፈርቱን የሚያሟላ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም

institution are accredited or renewed its accreditation.

15/ **"Limited Assessement"** shall mean an accreditation assessement conducted in some selected aspects of the accreditation standards after the institution or program is granted an accreditation with conditions.

16/ **"Accrediting body"** shall mean the Education and Training Authority or a reputable professional association or institution delegated by the authority to give accreditation.

17/ **"Person"** shall mean any natural person or an organ with legal personality

18/ Any expressions in masculine shall include feminine expression as well.

*3. <u>Scope of Application</u>*

This directive applies for any higher education institutions operating in Ethiopia

## *<u>Part two</u>*

## *<u>Structure, Roles and Responsibilities, Standards and procedures of Accreditation</u>*

*4. <u>The Accreditation</u>*

1) Any HEI fulfilling the accreditation standards can apply for institutional and program accreditation.
2) The HEI shall apply for accreditation using the prescribed application criteria should also attach self-evaluation reprt, student satisfaction survey and data

የተቋም እና የፕሮግራም እውቅና መጠየቅ ይችላል።

፪/ የእውቅና ማመልከቻ የሚያቀርብ ተቋም የግለ ግምገማ ሰነድ፣ የተማሪ እርካታ ዳሰሳ ሪፖርት እና የመረጃ መሰብሰቢያ ሪፖርት ማካተት/ማያያዝ ይኖርበታል።

፫/ የተቋም እና የፕሮግራም እውቅና ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው በካምፓስ ደረጃ ነው።

## ፭/ <u>ስለ እውቅና አሰጣጥ አደረጃጀት</u>

የእውቅና አሰጣጥ አደረጃጀት የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል

፩/ የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር

፪/ የእውቅና እና ስታንዳርዳይዜሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር

፫/ የእውቅና አሰጣጥ ካውንስል

፬/ እውቅና አሰጣጥ መሪ ሥራ አስፈጻሚ

፭/ የተቋምና የፕሮግራም እውቅና ዴስክ ኃላፊዎች

፮/ የተቋምና የፕሮግራም እውቅና አሰጣጥ ገምጋሚ ቡድን

## ፮/ <u>የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ተግባርና ሃላፊነት</u>

በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን በደንብ ቁጥር 515/2014 የተሰጠው ተግባርና

collection tool.

3) The application for institutional or program accreditation shall be made at a campus level

## 5. ***The Structure of Accreditation***

The structure of the Accreditation department shall be composed of:

1/ Director General of the Education and Training Authority

2/Deputy Director General of Accreditation and Standardization

3/The Accreditation Council

4/Chief Executive officer for Accreditation

5/Heads of the institutional and program accreditation Desk.

6/The institutional and program accreditation team of assessors.

## 6. ***Powers and Responsibilities of Director General, Education and Training Athority***

Without prejudice to the Powers and Responsibilities granted by Regulation No 515/2021, the Director General of Education and Training Authority shall:

1/Nominate members of the accreditation council out of ETA and establish appeal hearing committee;

2/Ensure that the accreditation decisions and other pertinent information have

ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፩/ ከባለስልጣኑ ውጪ የሚወከሉ የእውቅና ካውንስል አባላትን ይሰይማል እንዲሁም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴን ያቋቁማል፤

፪/ የእውቅና ውሳኔ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን ለተቋሙና ለማህበረሰቡ ተደራሽ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፤

፫/ ከእውቅና አሰጣጥ ግምገማና ውሳኔ ጋር በተያያዘ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚቀርቡ ቅሬታዎች በተዘረጋው የቅሬታ አፈታት ስርአት መሰረት እንዲፈቱ ያደርጋል፤

፬/ ለእውቅና ግምገማና ተያያዥ ጉዳዮች የፋይናንስና ግብዓት አቅርቦት እንዲመቻች ያደርጋል፤

፭/ የሙያ ማህበራት ተገምግመው በውክልና እውቅና እንዲሰጡ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡

## ፯/ የእውቅና እና ስታንዳርዳይዜሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተግባርና ኃላፊነት

በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን በደንብ ቁጥር 515/2014 የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

become accessible for the institution and the public access;

3/Ensure that complaints raised by HEIs pertaining to assessments and decisions on accreditation are dealt as per the grievance procedure in place;

4/Ensure that financial and material resources required to undertake accreditation processes and related issues are duly faciltated;

5/ Establish system and procedure that enable professional associations to participate in the accreditation process through delegation

## 7. ***Roles and Responsibilities of Deputy Director General for Accreditation and Standardization***

Without prejudice to the powers and responsibilities given to the Deputy Director General of Accreditation and Standardization by virtue of regulation No. 515/2022, the Deputy Director shall:

1/ Chair the accreditation council;

2/ Coordinate and control the institutional and program accreditation processes

3/ Announce decision made by the council to the authority and the HEIs and awards certificate to accredited institutions.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

፩/ የእውቅና ካውንስሉን በሰብሳቢነት ይመራል፤

፪/ የተቋምና የፕሮግራም እውቅና አሰጣጥ ሂደትንያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

፫/ የካውንስሉን ውሳኔ ለባለስልጣኑ እና ተቋማት ያሳውቃል፤ እንዲሁም እውቅና ላገኙ ተቋማት የእውቅና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

**፰/ <u>የእውቅና አሰጣጥ ካውንስል ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የእውቅና አሰጣጥ ካውንስል የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

፩/ የካውንስሉን የስራ መርሀ-ግብር ይነድፋል፤

፪/ በገምጋሚ ባለሙያዎች የሚቀርብን የተቋም እና የፕሮግራም እውቅና አሰጣጥ ሪፖርት እና የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ ያጸድቃል:

**፱/ <u>ስለካውንስሉ አባላት ብዛትና ስብጥር</u>**

ካውንስሉ ተጠሪነቱ ለትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ሆኖ ዘጠኝ አባላት ይኖሩታል። የካውንስሉ ዝርዝር አባላትና ስብጥር እንደሚከተለው ይሆናል።

፩/ የእውቅና እና ስታንዳርዳይዜሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር (ሰብሳቢ)።

፪/ የኢንስፔክሽን፣ የትምህርት ማስረጃ

**8. *<u>Roles and responsibilities of the Accreditation Council</u>***

The accreditation council shall have the following roles and responsibilities:

1/ Designs action plan for the accreditation council;

2/ Examines and approves the program accreditation decisions forwarded by the team of assessors

**9. *<u>Number and Composition of members of the Accreditation Council</u>***

The accreditation council, being accountable to the Director General of the Authority, shall be composed of the following nine members:

1/Dupty Director General for Accreditation and standardization (Chairperson)

2/ Dupty Director General for Inspection, authentication and Control (Member)

3/Chief Executive Officer of Accreditation (Member and Secretary)

4/ Chief Executive Officer of Quality Audit (Member)

5/ Representative of the Higher Education Division at Ministry of Education (Member)

6/ Four members appointed by the Director General of the authority based on criteria designated by the authority: one

ማረጋገጫና ቁጥጥር ምክትል ዋና ዳይሬክተር (አባል)፡፡

፫/ የእውቅና አሰጣጥ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ( አባልና ጸሃፊ)

፬/ የጥራት ኦዲት መሪ ሥራ አስፈጻሚ (አባል)፡፡

፭/ በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ተወካይ (አባል)፡፡

፮/ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ተመልምለው በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰየሙ አራት አባላት አንድ ከኢንዱስትሪ፣ አንድ ከሚመለከተው የሙያ ማኅበር (ለፕሮግራም እውቅና ብቻ)፣ አንድ ከመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና አንድ ከግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይሆናል፡፡

፯/ ለተቋም እውቅና በዚሁ አንቀጽ ካሉት አባላት በተጨማሪ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰየም አንድ ከሀገር አቀፍ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪ ተወካይ አባላት ይኖሩታል፡፡

፰/ በዚሁ አንቀጽ ላይ የተመለከቱት ከባለስልጣኑ ውጪ የሚመጡ የካውንስሉ አባላት የስራ ዘመን ሶስት አመት ሆኖ በድጋሚ ከተመረጡ ለተጨማሪ ሶስት አመታት የሚያገለግሉ ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ መመረጥ አይችሉም፡፡

፱/ ከተማሪ የተወከለው አባል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተወካይ ሆኖ እስከቆየ

from industries, one from the concerned professional association (for program accreditation only), one from public higher education institutions and the remaining one from private higher education institutions.

7/ For institutional accreditation, in addition to those listed under this artcle, there shall be one student representative of higher education institutions at a national level nominated by the Director General.

8/ The term of service of members of the council represented from outside of the authority shall be three years and can serve for three additional years if re-elected. No member shall be elected more than two terms.

9/A student represented from HEIs for the council shall serve as member of the council as long as he remains a higher education institution representative

***10. <u>Roles and Responsibilities of the Secretary of the Accreditation Council</u>***

1/Executes the decisions of the accreditation council and reports its implementation to the council;

2/ Supports the regular activities of the accreditation council;

3/ Holds minutes for each and every decision of institutional and program

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ድረስ የሚቆይ የአገልግሎት ዘመን ይኖረዋል፡፡

**፲/ <u>የእውቅና አሰጣጥ ካውንስል ፀሀፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

፩/ የካውንስሉን ውሳኔ ያስፈጽማል፤ ስለአፈጻጸሙም ለካውንስሉ ሪፖርት ያቀርባል፤

፪/ የእውቅና ካውንስሉን መደበኛ ተግባራት ይደግፋል፤

፫/ ለእያንዳንዱ የተቋምና የፕሮግራም እውቅና ውሳኔዎች ቃለ-ጉባዔ ይይዛል፡፡

**፲፩. <u>የእውቅና ካውንስል ስብሰባዎች</u>**

፩/ የእውቅና ካውንስሉ በዓመት አራት ጊዜ መደበኛ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፡፡ የእውቅና ካውንስሉ አባላት አጠቃላይ የስብሰባውን ሂደት ሊወስኑ ይችላሉ፤

፪/ በዚህ አንቀጽ "1" ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የእውቅና ካውንስል ሰብሳቢው እንደ አስፈላጊነቱ ልዩ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

፫/ ካወንስሉ ለውሳኔ በሚሰበሰብበት ጊዜ የካውንስሉ ስብሰባ መካሄድ የሚችለው ሃምሳ በመቶ ሲደመር አንድ አባላት ሲገኙ ነው፤

፬/ የካውንስሉ አባላት ድምጽ-ውሳኔ እኩል ድምጽ በሚሆንበት ጊዜ የካውንስሉ ሰብሳቢ ያለበት ድምጽ-ውሳኔ የጸና

accreditation

**11. <u>Meetings of the Accreditation Council</u>**

1/ The accreditation council's ordinary meetings shall be held four times a year. Members of the accreditation council shall decide the council's meeting schedule

2/ Without prejudice to the provision of sub article 1of this artcle, the council chairperson shall arrange a extra-ordinary meeting as it deemed necessary.

3/ The accreditation council meeting shall be conducted only when 50%+1 members attend.

4/ Where equal number of votes are made for competing motions of the council decision, the motion voted by the chairperson of the council takes precedence.

**12. <u>Termination of membership of the Accreditation Council</u>**

Membership of the accreditation council may terminate due to one of the following conditions:

1/By willfull resignation of a member;

2/ Due to disciplinary cases;

3/Unexcused absence from meetings for three consecutive meeting sessions.

**13. <u>Roles and Responsibilities of Chief Excutive for Accreditation</u>**

Without prejudice to those granted to him by the authority, Chief Excutive for accreditation shall

ይሆናል፡፡

**፲፪. <u>የእውቅና ካውንስል አባልነትን ስለማቋረጥ</u>**

የካውንስል አባልነት በሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊቋረጥ ይችላል፡፡

፩/ በፈቃዳኝነት ከአባልነት ሲለቅ፤

፪/ የስነስርዓት ጉድለት ሲፈጽም፤

፫/ በስብሰባዎች ላይ ያለፍቃድ ከሶስት ጊዜ በላይ ሲቀር፡፡

**፲፫. <u>የእውቅና አሰጣጥ መሪ ስራ አስፈጻሚ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የእውቅና አሰጣጥ መሪ ስራ አስፈጻሚ ተግባርና ኃላፊነት በባለስልጣኑ የተሰጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፤

፩/ የእውቅና የግምገማ ረቂቅ ሪፖርት ለካውንስሉ ያቀርባል፤ውሳኔውን ያስፈጽማል፤

፪/ በየዓመቱ የጥራት ማሻሻልና ክትትል ሪፖርት ከተቋማት ተቀብሎ ይመረምራል፤

፫/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ልዩ ግምገማ እንዲካሄድ ያደርጋል፤

፬/ በካውንስሉ ውሳኔ መሰረት ውስን ግምገማ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

**፲፬. <u>የእውቅና አሰጣጥ ዴስክ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

have the following Roles and Responsibilities:

1/ Presents the accreditation draft report to accreditation council; implements the decision;

2/ Recieves and examines quality improvement and follow up report of institutions each year;

3/ shall enforce conducting a special assessment as deemed necessary;

4/Undertakes limited assessement based on the council's decision.

**14. <u>Roles and Responsibilities of Head of the Accreditation Desk</u>**

Without prejudice to those granted to him by the authority, Head of the Accreditation Desk shall have the following roles and responsibilities:

1/ Organizes the accreditation team of assessers in accordance with the criterion put in place;

2/ Examines the accreditation applications, Data collection tools, student satisfaction survey reports and self evaluation Report to the team of assessors; Dispatches team of assessors for field visit and coordinates the field visit activities;

3/ Examines the accreditation assessment report prepared by the team of assessors and presents it to chief executives for accreditation.

የእውቅና አሰጣጥ ዴስክ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት በባለስልጣኑ የተሰጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፩/ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የእውቅና ገምጋሚ ቡድን ያደራጃል፤

፪/ የእውቅና ጥያቄ ማመልከቻዎችን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሪፖርት፣ የተማሪ እርካታ ዳሰሳ ሪፖርት እና የግለግምገማ ሰነድ ይመረምራል፤ ለመስክ ብቁ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ለገምጋሚ ቡድን ይመራል፤ የግምገማ ቡድን ያሰማራል፤ የመስክ ጉብኝትን ያስተባብራል፤

፫/ በገምጋሚ ቡድን ተዘጋጅቶ የቀረበን የእውቅና ሪፖርት ካጣራ በኂላ ለእውቅና አሰጣጥ መሪ ስራ አስፈጻሚ ያቀርባል፡፡

**፲፭. <u>የእውቅና አሰጣጥ ገምጋሚ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የእውቅና ገምጋሚ ቡድን የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፩/ የቀረቡትን የእውቅና ጥያቄ ማመልከቻ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሪፖርት፣ የተማሪ እርካታ ዳሰሳ ሪፖርት እና የግለግምገማ ሰነድን ይመረምራል፤

፪/ የእውቅና ግምገማ የጊዜ ሰሌዳን ያዘጋጃል፤ የመስክ ግምገማን ያካሄዳል፤

፫/ የመስክ ግምገማውን ሲያጠናቅቅ

**15. <u>Roles and Responsibilities of the Accreditation Team of Assessors</u>**

1/ Examine the accreditation application document, data collection tools report, student satisfaction survey report and self-evaluation Report.

2/ Prepares schedule for accreditation assessment; undertake field examination.

3/ Submits exit report regarding the assessment process for the institution up on the completion of the assessment work.

4/ Produces the assessment report and submits it to Head of the Desk.

5/ Determine the detailed roles and responsibilities of the team of assessors as well as their recruitment procedures as per the guidelines and work procedures of the authority.

**16. <u>Number and Composition of the Members of Team of Assessors</u>**

1/ The accreditation team of assessors shall be composed of five members.

2/ Three members of the team of assessors shall be selected from the authority's accreditation experts while the remaining two members are selected from HEIs, from industries or from representatives of concerned professional associations.

3/ One of the members from the authority shall be chairperson.

4/ The team of assessors shall select a

ለተገምጋሚው ተቋም ስለ ግምገማው ሂደት የመውጫ ሪፖርት በጽሁፍ ይሰጣል፤

፬/ የግምገማ ሪፖርት በማዘጋጀት ለዴስክ ኃላፊ ያቀርባል፤

፭/ ዝርዝር የገምጋሚ ቡድኑ ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም የቡድን አባላት አመራረጥ በባለሥልጣኑ የአሠራር ሰርዓት ይወሰናል።

**፲፮. የገምጋሚ ቡድን አባላት ብዛትና ስብጥር**

፩/ የእውቅና አሰጣጥ ገምጋሚ ቡድን አምስት አባላት ይኖሩታል

፪/ የገምጋሚ ቡድኑ አባላት ሶስት ከባለስልጣኑ የእውቅና አሰጣጥ ባለሙያዎች፣ አንድ ተባባሪ ባለሙያ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና አንድ ከኢንዱስትሪ ወይም ከሚመለከተው የሙያ ማህበር ተወካይ ይሆናል፤

፫/ ከባለስልጣኑ ባለሙያዎች አንዱ ሰብሳቢ ይሆናል፤

፬/ ቡድኑ ከአባላቱ መካከል ጸሐፊ ይመርጣል፤

፭/ ዝርዝር የገምጋሚ ቡድኑ አመራረጥና ስልጠና ሌሎች የአሠራር ሰነዶች ይወጡለታል።

**፲፯. ስለ ስታንዳርዶች**

፩/ የተቋም እውቅና ስታንዳርዶች

secretary from amongst themselves.

5/ Guidelines shall be developed for the detailed selection criteria and trainings of the team of assessors.

**17. Standards**

1/ Standards of Institutional accreditation

a) Vision, Mission and Governance

b) Curriculum and Program Management

c) Learning and Teaching

d) Assessment and Evaluation

e) Students

f) Academic and Support Staff

g) Resources

h) Research and Community Engagemnt

i) Continual Quality Improvement

2/ Standards of Program accreditation

a) Program Outcome

b) Curriculum

c) Learning, Teaching and Assessment

d) Students

e) Academic Staff

f) Educational Resources

g) Research and Community Engagemnt

h) Program Management

i) Continual Quality Improvement

**18. The Accreditation Procedure**

**1/** The accreditation Application Procedures

ሀ) ራእይ፣ ተልእኮ እና አስተዳደር

ለ) ስርአተ ትምህርት እና የፕሮግራም አመራር/አስተዳደር

ሐ) መማር ማስተማር

መ) ምዘናና ግምገማ

ሠ) ተማሪዎች

ረ) መምህራን እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

ሸ) የትምህርት ግብዓት

ቀ) ምርምር እና ማህበረሰብ ጉድኝት

በ) ቀጣይነት ያለው የጥራት ማሻሻያ ስርአት

፪/ የፕሮግራም እውቅና ስታንዳርዶች

ሀ) የፕሮግራም ውጤት

ለ) ስርአተ ትምህርት

ሐ) መማር ማስተማር እና ምዘና

መ) ተማሪዎች

ሠ) መምህራን

ረ) የትምህርት ግብዓት

ሸ) ምርምር እና ማህበረሰብ ጉድኝት

ቀ) የፕሮግራም አመራር/አስተዳደር

በ) ቀጣይነት ያለው የጥራት ማሻሻያ ስርአት

**፲፰. <u>የእውቅና አሰጣጥ የአሠራር ሂደት</u>**

፩/ የእውቅና ጥያቄ አቀራረብ

ሀ) የተቋም ወይም የፕሮግራም እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ከግለ-ግምገማ ሪፖርት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሪፖርት እና የተማሪ እርካታ

a) Institutional or program accreditation application shall be submitted together with self Assessment report, data collection tools report and the student satisfaction survey report.

b) The accreditation application shall be prepared as per ETA's accreditation application formats and will be submiited manually or in a digital system.

**2/ The Document review**

a) Head of the desk shall examine the accreditation application documents submitted by the institutions and ensure that it is eligble for field visit.

b) Head of the desk shall organize a team of assessors and communicates them to the institution in accreditation process to ensure that there is no conflict of interest.

c) The desk head shall Identifythe accreditation application documents that are not eligble for field visit and informs them to the institutions.

**3/ The Field Visit**

a) The organized team of assessors shall conduct field visit as per the delineated time table.

c) The team of assessors shall validate by field visit the findings obtained

ዳሰሳ ሪፖርት ጋር አብሮ ይቀርባል፤

ለ) የእውቅና ማመልከቻው ባለስልጣኑ በሚያስቀምጠው የእውቅና ጥያቄ አቀራረብ ስርዓት ማለትም በዲጅታል ወይም በማንዋል ሆኖ በጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ መስረት ይሆናል፤

፪/ የሰነድ ምርመራ

ሀ) የዴስክ ሀላፊው የቀረበውን የእውቅና ማመልከቻና ሰነዶችን በመመርመር እና በማጣራት ለመስክ ጉብኝት ብቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) የዴስክ ሀላፊው የገምጋሚ ቡድን በማደራጀት የቡድኑን አባላት ለተገምጋሚው ተቋም በማሳወቅ የጥቅም ግጭት ስለመኖሩ እና ስለአለመኖሩ ያረጋግጣል፤

ሐ) ለመስክ ጉብኝት ብቁ ሆነው ያልተገኙ የእውቅና ማመልከቻ እና ሰነዶችን ለተቋሙ ያሳውቃል፤

፫/ የመስክ ጉብኝት

ሀ) የተቋቋመው ገምጋሚ ቡድን በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የመስክ ጉብኝት ያካሄዳል፤

ለ) ገምጋሚ ቡድኑ በሰነድ ማጣራት እና ጥናት ያገኛቸውን ግኝቶች በመስክ ግምገማ ያረጋግጣል፤

ሐ) ገምጋሚ ቡድኑ ግምገማውን የሚያጠናቅቀው ስላካሄደው ግምገማ

from thorough examination of the application documents.

c) The team of assessors shall finalize the assessment process up on conducting an exit meeting and submitting the exit report to the institutiton.

**4/ The Accreditation Report Preparation**

a) The accreditation report shall be prepared as per the authority's report preparation guideline and report format based on the information and data obtained from the self evaluation report, data collection tools report, students'satisfaction survey report and the field visit.

b) The chairperson of the team of assessors together with the accreditation desk officer shall submit the accreditation report to the chief executive officer for accreditation.

**5/ The Accreditation Decision Process**

a) The Chief Executive Officer for accreditation shall submit the assessment report to the accreditation council.

b) Chairperson of the team of assessors shall present the assessment report to the council.

c) The accreditation council shall pass the accreditation decision up on examining the accreditation report.

የመውጫ ውይይት በማድረግ የመውጫ ሪፖርቱን ለተቋሙ በጽሁፍ በማሳወቅ ይሆናል።

፬/ ሪፖርት ዝግጅት

ሀ) የመስክ ግምገማ ሪፖርት የሚዘጋጀው በባለስልጣኑ የሪፖርት አዘገጃጀት መምሪያ መሰረት ሆኖ ከግለ-ግምገማ ሪፖርት፣ ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሪፖርት፣ ከተማሪ እርካታ ዳሰሳ ሪፖርት እና ከመስክ ጉብኝት በተረጋገጠ ግኝት መሰረት ይሆናል፤

ለ) የገምጋሚ ቡድኑ ሰብሳቢ ከዴስክ ኃላፊው ጋር ሆኖ የቀረበውን ሪፖርት መርምሮ ለእውቅና አሰጣጥ መሪ ስራ አስፈጻሚ ያቀርባል።

፭/ የውሳኔ አሰጣጥ

ሀ) የእውቅና አሰጣጥ መሪ ስራ አስፈጻሚ የእውቅና ሪፖርትን ለእውቅና ካውንስሉ ሰብሳቢ ያቀርባል፤

ለ) የገምጋሚ ቡድኑ ሰብሳቢ የግምገማ ሪፖርቱን ለካውንስሉ ያቀርባል፤ ገለጻ ያደርጋል፤

ሐ) የእውቅና ካወንስሉ የቀረበለትን የእውቅና ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ ያሳልፋል፤

መ) የካውንስሉ ሰብሳቢ በካውንስሉ የተላለፈውን ውሳኔ ውጤቱን ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክቴር እና

d) Chairperson of the accreditation council shall announce result of the accreditation decision given by the council to the Director General of the authority and the institutions and awards the accreditation certificate to the accredited institution as well.

**19. Accreditation Decision and Duration**

Based on the findings of the accreditation assessment conducted, the HEIs institutional and program accreditation decisions shall be:

**1/ Full Accreditation**

a) Is an accreditation granted to an institution or a program for a period of five years based on the accreditation assessment result of the institution or program falls in the highest category of the accreditation result cut off point stated in the guideline

**2/ Accreditation with condition**

a) Is an accreditation granted to an institution or a program for a period of three years based on the accreditation assessment result of the institution or program when its assessment result falls in the medium category of the accreditation result cut off point stated in the guideline.

**3/ Denial of Accreditation**

a) The institution shall be denied accreditation when the institution's assessment result falls within the the lowest category of the accreditation result cut off point guideline set by the authority.

b) The institution or program which is denied accreditation shall re-apply for accreditation one year after the date of denial of accreditation.

ለተቋማት ያሳውቃል፤ እንዲሁም እውቅና ላገኘ ተቋም የእውቅና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

**፲፱. <u>የእውቅና ውሳኔ እና የቆይታ ጊዜ</u>**

ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቋም እና የፕሮግራም እውቅና የሚሰጥ ውሳኔ በግምገማው ውጤት መሰረት፦

፩/ ሙሉ እውቅና

በተደረገው የእውቅና ግምገማ ተቋሙ ወይም ፕሮግራሙ ያገኘው ውጤት በባለስልጣኑ በወጣው የውጤት መወሰኛ መምሪያ መሰረት ከፍተኛ ውጤት ክልል ውስጥ ሲገኝ ለአምስት ዓመት የሚሰጥ ይሆናል፤

፪/ በሁኔታ የተገደበ እውቅና

በተደረገው የእውቅና ግምገማ ተቋሙ ወይም ፕሮግራሙ ያገኘው ውጤት በባለስልጣኑ በወጣው የውጤት መወሰኛ መምሪያ መሰረት መካከለኛ ውጤት ክልል ውስጥ ሲገኝ ለሶስት ዓመት የሚሰጥ ይሆናል።

፫/ የእውቅና ክልከላ

ሀ) በተደረገው የእውቅና ግምገማ ተቋሙ ወይም ፕሮግራሙ ያገኘው ውጤት በባለስልጣኑ በወጣው የውጤት መወሰኛ መምሪያ መሰረት በተቀመጠው ዝቅተኛ የውጤት ክልል ውስጥ ሲገኝ የሚከለከል ይሆናል፤

**20. <u>Cancellation of Accreditation</u>**

The authority shall reassess the institution's accreditation decision any time and shall get its accreditation cancelled for either of the following reasons:

a) Where the institution or program fails to maintan the systems and resources that were in place during the assessment time.

b) Where the institution or program fails to request renewal of accreditation within the proper time range.

c) Where it is proved by evidence that the institution or the program has violated the legal procedures put in place by the authority.

**21. <u>Special Assessment</u>**

Conditions that necessitate a special accreditation assessment:

1/ Where the ministry of education or any other appropriate authority amends the educational system or policy;

2/ Where there is proof and evidence indicating that the accreditation granted to the program or institution is erroneous/ faulty.

**22. <u>Limited Assessment</u>**

Conditions that necessitate partial (limited) accreditation assessment:

1/ Conducted to prove that the institution or the program which has been granted an accreditation on condition has addressed areas of improvement suggested by the time preconditions have been addressed.

2/ To promote an institution or a program

Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

ለ) የተቋም ወይም የፕሮግራም እውቅና የተከለከለ ተቋም ዳግም የእውቅና ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ክልከላው ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል።

**፳. <u>እውቅናን ስለመሰረዝ</u>**

ባለስልጣኑ የተቋሙን ወይም የፕሮግራሙን የእውቅና ውሳኔ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ይመረምራል፤ ተቋሙ ወይም ፕሮግራሙ ከሚከተሉት ተግባራት ውስጥ አንዱን አንድሎ ቢገኝ በግኝቱ መሰረት እውቅናው ይሰረዛል።

፩/ ተቋሙ ወይም ፕሮግራሙ ህጋዊ እውቅና ያገኘበትን አሰራርና ጥራት አስጠብቆ መቀጠል ካልቻለና ይህም በግምገማ ከተረጋገጠ፤

፪/ እውቅና አግኝቶ ሲሰራ የቆየ ተቋም ወይም ፕሮግራም የእውቅና እድሳቱን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልጠየቀ፤

፫/ ባለስልጣኑ ያስቀመጣቸውን የህግ ጥሰቶች ፈጽሟል ተብሎ ማስረጃ ከቀረበና ከታመነ።

**፳፩. <u>ስለ ልዩ ግምገማ</u>**

የእውቅና ግምገማ በልዩ ሁኔታ ግምገማ እንዲካሄድ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች

፩/ ሚኒስትሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል የትምህርት ስርዓቱን በፖሊሲ

which has been granted an accreditation on conditions to full accreditation up on ensuring that ares of improvement previously suggested have been addressed.

## PART THREE

## PRECONDITIONS FOR INSTITUTIONAL AND PROGRAM ACCREDITATION

**23. <u>Institutional Accreditation preconditions</u>**

Any institution may apply for institutional accreditation only upon fulfilling the following preconditions:

1/ The institution shall have a teaching license in higher education from the authority or shall be established by any federal or regional government authority to operate in the higher education sector.

2/ The institution must have graduated students at least once in one program.

3/ The institution must have undergone institutional quality audit by the authority prior to application for institution accreditation.

4/ The institution must have paid the accreditation fee designated by the authority for institution accreditation.

**24. <u>Precondition for Program Accreditation</u>**

Any institution may apply for program accreditation only upon fulfilling the following

ወይም አግባብነት ባላቸው ህጎች ሲያሻሽለው፤

፪/ ለተቋሙ የተሰጠው የተቋም ወይም ፕሮግራም እውቅና ጉድለት አለበት ተብሎ በመረጃና ማስረጃ የተደገፈ ጥቆማ የሚቀርብ ከሆነ፡፡

**፳፪. <u>ስለ ውስን ግምገማ</u>**

ውስን የእውቅና ግምገማ እንዲካሄድ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች

፩/ ተቋሙ ወይም ፕሮግራሙ በሁኔታ የተገደበ እውቅና ያለው ሆኖ በሪፖርቱ ላይ የተገለጹትን የጥራት ጉድለቶች ስለማሻሻሉ በግምገማ ለማረጋገጥ፤

፪/ በሪፖርቱ ላይ የተገለጹትን የጥራት ጉድለቶች ስለማሻሻሉ በግምገማ በማረጋገጥ በሁኔታ የተገደበ የተቋሙን ወይም የፕሮግራሙን እውቅና ወደ ሙሉ እውቅና ለማሳደግ፡፡

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>ስለ ተቋም እና ፕሮግራም እውቅና አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታዎች</u>**

**፳፫. <u>የተቋም እውቅና ቅድመ ሁኔታ</u>**

ማንኛውም ተቋም የተቋም እውቅና ሊጠይቅ የሚችለው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ሲችል ብቻ ነው፡፡

፩/ ተቋሙ ከባለስልጣኑ በከፍተኛ

preconditions:

1/ The institution must have avalid teaching license in the program granted by the authority.

2/ The institution shall apply for program accreditation only in the modality and level for which it is licensed

3/ The institution must have graduated at least one batch in the program;

4/ The institution must have paid the fee designated by the authority for program accreditation.

**<u>PART FOUR</u>**

**<u>RE-ACCREDITATION</u>**

**25. <u>Institution and Program Re-accredittion Process</u>**

1/ The procedures and processes mentioned in article 17 shall apply for of institutional and program re-accreditation.

2/Without prejudice to those preconditions mentioned in section three, the following points shall be used as preconditions for renewal of institutional accreditation:

3/ Any institution shall meet the following preconditions in order to apply for renewal of institutional accreditation.

a) The institution must be accredited and must have a renewalal of teaching license.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ትምህርት የማስተማር ፈቃድ ያለው ወይም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ እንዲሰራ በፌደራል ወይም በክልል መንግስታት ስልጣን ባለው አካል የተቋቋመ ሊሆን ይገባል፤

፪/ ተቋሙ ቢያንስ በአንድ ፕሮግራም አንድ ዙር ያስመረቀ መሆን ይገባዋል፤

፫/ ተቋሙ የተቋም እውቅና ከመጠየቁ በፊት በባለስልጣኑ ተቋማዊ ጥራት ኦዲት ያካሄደ መሆን አለበት፣

፬/ ተቋሙ በባለስልጣኑ ለተቋም እውቅና አሰጣጥ ሥራ የተቀመጠውን የክፍያ መጠን መክፈል ይኖርበታል።

**፳፬. <u>የፕሮግራም እውቅና ቅድመ ሁኔታ</u>**

ማንኛውም ተቋም የፕሮግራም እውቅና ሊጠይቅ የሚችለው የሚከተሉትን ማሟላት ሲችል ብቻ ነው።

፩/ ተቋሙ ከባለስልጣኑ በፕሮግራሙ የማስተማር ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፤

፪/ ተቋሙ የፕሮግራም እውቅና ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ፈቃድ ባገኘበት አግባብና ደረጃ መሆን ይገባዋል፤

፫/ ተቋሙ በፕሮግራሙ ቢያንስ አንድ ዙር ተማሪዎችን ያስመረቀ መሆን ይገባዋል፤

፬/ ተቋሙ በባለስልጣኑ ለፕሮግራም እውቅና አሰጣጥ ሥራ የተቀመጠውን የክፍያ መጠን መክፈል ይኖርበታል።

b) Renewal of institutional accreditation is undertaken only up on the expiration of the previous accreditation period.

c) The institution is expected to provide reports and supportive evidances of the improvements made and the activities conducted based on successive previous accreditations.

d) Any institution shall submit its application for renewal of institutional accreditation six months ahead of the expiration of the previous accreditation period.

4/ The institutional accreditation renewal assessment shall be conducted based on the institutional accreditations standard mentioned in article 17(1) to assess the institution.

5/ The program re-accreditation assessment shall be conducted based on the institutional accreditations standard mentioned in article 17(2) to assess the institution.

**26. <u>Decisions and Durations of Re-accreditation</u>**

Based on the findings of the accreditation assessment conducted, the HEIs institutional and program re-accreditation decisions shall be:

1/ Re-accreditation

a) Is granted to an institution or a

## ክፍል አራት

## እውቅና እድሳት

**፳፮. ስለተቋም እና ፕሮግራም እውቅና እድሳት የአሰራር ሂደት**

፩/ ለተቋም እና ለፕሮግራም እውቅና እድሳት በአንቀጽ 17 የተገለጹት የአሰራር ሂደቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፤

፪/ በክፍል ሶስት ላይ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦችም ለተቋም እና ፕሮግራም እውቅና እድሳት እንደ ቅድመ ሁኔታ ሆነው ያገለግላሉ።

፫/ የተቋም እና ፕሮግራም እውቅና እድሳት ጥያቄን ለማቅረብ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል።

ሀ) እውቅና እና የታደሰ ፈቃድ፤

ለ) እውቅናው ወይም እውቅና እድሳቱ ሲያበቃ፤

ሐ) እውቅናው ከተሰጠ ጊዜ ጀምሮ የተደረጉ ማሻሻያዎች እና የተከናወኑ ተግባራትን የሚያሳይ ሪፖርትና ማስረጃ ሲቀርብ እና

መ) የእውቅና ጊዜው ከመጠናቀቁ ስድስት ወር በፊት እውቅና እድሳት ሲጠይቅ ይሆናል።

፬/ የተቋም እውቅና እድሳት ግምገማ

program for a period of five years based on the re-accreditation result cut off point guideline set by the authority.

2/ Denial of re-accreditation

a) The institution or the program may be denied re-accreditation where the institution's or program's assessment result falls within the the lowest category of the accreditation result renewal cut off point guideline set by the authority.

b) The institution or program which is denied renewal of accreditation may re-apply for re-accreditation one year after the first date of denial.

**27. Follow up for Quality**

1/ The accredited institution or program shall submit annual reports indicating that it has properly implemented the areas of improvement stated in the accreditation report and is working on the continual quality improvement activities as well.

2/ The authority shall follow up the institution based on the report and conduct special field assessment when deemed necessary.

**28. Accreditation benefits**

1/ The Ministry of Education may provide the following benefits to accredited institutions and programs

a) Special placement of students

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

የሚካሄደው የተቋም እውቅናን ለመገምገም በአንቀጽ 17(1) ላይ በተገለጸው መሰረት ይሆናል፡፡

፫/ የፕሮግራም እውቅና እድሳት ግምገማ የሚካሄደው የፕሮግራም እውቅናን ለመገምገም በአንቀጽ 17(2) ላይ በተገለጸው መሰረት ይሆናል፡፡

**፳፮. <u>የእውቅና እድሳት ውሳኔ እና የቆይታ ጊዜ</u>**

ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቋም እና የፕሮግራም እውቅና እድሳት የሚሰጥ ውሳኔ በግምገማው ውጤት መሰረት፦

፩/ እውቅና እድሳት

ሀ) በተደረገው የእውቅና እድሳት ግምገማ ተቋሙ ወይም ፕሮግራሙ ያገኘው ውጤት በባለስልጣኑ በወጣው የውጤት መወሰኛ መምሪያ መሰረት ለአምስት ዓመት የሚታደስለት ይሆናል፡፡

፪/ የእውቅና እድሳት ክልከላ

ሀ) በተደረገው የእውቅና እድሳት ግምገማ ተቋሙ ወይም ፕሮግራሙ ያገኘው ውጤት በባለስልጣኑ በወጣው የውጤት መወሰኛ መምሪያ መሰረት በተቀመጠው ዝቅተኛ የውጤት ክልል ውስጥ ሲገኝ የእውቅና እድሳቱ የማይታደስለት

b) Allocating a special budget for research activities

c) Providing special scholarships to the academic staff and students of the institution and or program.

d) Advertising accredited institutions and or programs together with the Authority

e) Support to create linkages with different industries or stakeholders in a special way.

## PART FIVE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**29. <u>Rights and Responsibilities of the HEIs</u>**

**1/ Rights of Institutions**

a) Institutions shall have the right to request training services from the authority regarding the accreditation process, self assessment Report preparation and quality assurance system in general.

b) Any institution has the right to know the accreditation assessment schedule after submitting application for accreditation.

c) An institution which is denied accreditation shall have the right to appeal the decision to the authority in accordance with the grievance resolution procedures in

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ይሆናል፡፡

ለ) የተቋም ወይም ፕሮግራም እውቅና እድሳት የተከለከለ ተቋም ዳግም የእውቅና እድሳት ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ክልከላው ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

**፳፯. ስለ ጥራት ክትትል**

፩/ እውቅና ያገኘ ተቋም ወይም ፕሮግራም እውቅና ሪፖርት ላይ የተገለጹትን የጥራት ጉድለቶችን ስለማሻሻሉ ለማረጋገጥ የሚያስችል የማሻሻያ እቅድ እና ሪፖርት በየዓመቱ ይልካል፤

፪/ በሪፖርቱ መሰረት ባለስልጣኑ ክትትል ያደርጋል፤ በአካል በመገኘትም ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡

**፳፰. <u>ስለእውቅና ማበረታቻዎች</u>**

፩/ የትምህርት ሚኒስቴር እውቅና ለተሰጣቸው ተቋማትና ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ማበረታቻዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሀ) ተማሪን በልዩ ሁኔታ መመደብ፤

ለ) ለጥናትና ምርምር በልዩ ሁኔታ በጀት መመደብ፤

ሐ) ለተቋሙ መምህራንና ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ የትምህርት እድል መስጠት፤

place.

2/ **Responsibilities of the Institutions**

a) The higher education institution under evaluation shall provide all pertinent documents to the team of assessors and should give keen response to any question raised by the team of assessors.

b) The institution shall provide all kinds of support to the team of assessors during the field visit.

**30. <u>Grievance Procedure and Resolution System</u>**

The accreditation grievance hearing committee shall be nominated by the Director General, and rules of procedures addressing the number and composition of the committee, process and procedures of grievance resolution, time and manner of decision shall be developed for its implementation.

**31. <u>inapplicable laws</u>**

Any directive, administrative decision or customary practices which are contrary to this directive shall not be applicable with regard to the provisions of this directive.

**32. <u>Amendment of the Directive</u>**

The ministry of education may amend the directive at any time where it is deemed necessary.

Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

መ) ከባለስልጣኑ ጋር በመሆን የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም እውቅና ያላቸውን ተቋማት ወይም ፕሮግራም ማስተዋወቅ፤

ሠ) ከተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ወይም ባለድርሻ አካላት ጋር በልዩ ሁኔታ ትስስር እንዲፈጥሩ ድጋፍ ማድረግ፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፴፱. ስለ ተቋማት መብትና ግዴታዎች

፩/ የተቋማት መብት

ሀ) ተቋማት ስለ እውቅና አሰጣጥ ሂደት፣ ስለግለ-ግምገማ ዝግጅትና ስለትምህርት ጥራት አጠባበቅ በአጠቃላይ ከባለስልጣኑ ስልጠና ሲያስፈልጋቸው የስልጠና ድጋፍ ጠይቀው ማግኘት ይችላሉ፤

ለ) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማመልከቻ ካቀረበ በኂላ የእውቅና ግምገማ ጊዜ መርሀግብሩን የማወቅ መብት አለው፤

ሐ) እውቅና የተከለከለ ተቋም በቅሬታ አፈታት መምሪያ መሰረት ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ የተቋማት ግዴታ

### 33. Effective date

This directive shall be effective as of the date registered with the ministry of justice and its uploading on the official website of the ministry of education.

**Addis Ababa, 2024**

**Berhanu Nega (Professor)**

**Minister, Minstry of Education of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

ሀ) ተቋሙ ለገምጋሚ ባለሙያዎች ቡድን መረጃ እና ማስረጃ ማቅረብ እና የቡድኑ አባላት ለሚያነሷቸው ተያያዥ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ይኖርበታል፤

ለ) ተቋሙ ግምገማው በሚከናወንባቸው ቀናት ውስጥ ገምጋሚ ቡድኑ ለሚያደርጋቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል።

## ፴. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት

የእውቅና አሰጣጥ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የሚሰየም ሆኖ ባለስልጣኑ በሚዘጋጀው የአሰራር ስርአት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ቁጥር እና ስብጥር፣ የአሰራር ሂደት፣ ውሳኔ የሚሰጥበት ጊዜና አግባብ የሚዳሰስ ሲሆን በመምሪያው ላይ በተቀመጠው መሰረት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል:

## ፴፩. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ የአስተዳደር ውሳኔ እና የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## ፴፪. መመሪያውን ስለማሻሻል

የትምህርት ሚኒስቴር መመሪያውን አስፈላጊ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**፴፫. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትምህርት ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ 2016**

**ብርሀኑ ነጋ ( ፕሮፌሰር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር**